**ለበለጠ መረጃ ወይም ለቃለ መጠይቅ ለመጠየቅ እባክዎ ያነጋግሩ:**

ሚሼል ጌይስ ዋላስ:- mgeis@burness.com; +254 711 326 770

ዴቪድ አሮንሰን:- d.aronson@cgiar.org; +254 717 868 916

ዶ/ር ጌትነት መኩሪያው ስ.ቁ: +251946951236

email: getinet.mekuriaw.tarekegn@slu.se

ዶ/ር ታደለ ደሴ ስ.ቁ: +251 944720210

email: t.dessie@cgiar.org

**ማስታወሻ:-** ጥናቱን እና ፎቶዎችን ጨምሮ ሁሉም ተዛማጅ መረጃዎች ማስፈንጠሪያውን በመጫን ማግኘት ይቻላል: https://burness.com/press-room/nature-genetics-paper (የይለፍ ቃል *nature*)

**ቀነ ገደብ**

**እስከ መስከረም 18 ቀን 2013 ዓ.ም. በናይሮቢ ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ12:00 ፣ በሎንዶን ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ 10:00 እንዲሁም በኒውዮርክ ሰዓት አቆጣጠር ከጥዋቱ 5:00 ሰዓት ድረስ በአታሚው ድርጅት ወይም መፅሄት አማካኝነት እስከሚለቀቅ በዕገዳ ላይ ይቆያል።**

# የአፍሪካ አርብቶ አደሮች የ ሺ ዓመታት የዳልጋ ከብቶች አረባብ ዘዴን እና ከፍተኛ ሙቀትን፥ ድርቅንና በሽታን መቋቋም የሚያስችሉ የዘር ውርስ ባህሪያት እንደተለዩ አዲስ ጥናት አመለከተ!

**(ናይሮቢ ፣ ኬንያ ፣ መስከረም 18 ቀን 2013**) - የሳይንስ ጠበብቶች ሙቀት እና ድርቅ ፥ እንደ ገንዴ ያሉ ገዳይ በሽታዎችን መቋቋምና መኸገርን መቆጣጠር የሚያስችሉ አዳዲስ የዘረመል ቅንጣቶችን በአፍሪካ የዳልጋ ከብቶች እንዳገኙ በዛሬው ዕለት አስታወቁ።

የተፈጥሮ ዘረመል (*Nature Genetics Journal*) መፅሔት በጥቅምት ወር ዕትሙ ይዞት የወጣው የምርምር ግኝት እንደሚያሳየው የአፍሪካ የዳልጋ ከብቶች በተለያዩ ክፍላተ-አህጉሩ ላለፉት ዕስራ ዓዕማት ተወስነው ሲኖሩ የራሳቸውን መራሔ ባህሪያት እንዲያዳብሩ እንዳስቻላቸው በ172 የዳልጋ ከብቶች ሙሉ ዘረመል ትንተና (Whole Genome Sequencing) ላይ የተካሄደው ጥናት አመላክቷል። ጥናቱ ከተለያዩ ዓለም አቀፍ

ተቋማት ማለትም አዲስ አበባ እና ናይሮቢ ከሚገኘው ዓለም አቀፍ የእንስሳት ምርምር ተቋም(ILRI)፥ ከሰዑል ናሽናል ዩኒቨርስቲ (ደቡብ ኮርያ)፥ ከደቡብ ኮርያ የገጠር ልማት ኤጀንሲ (RDA, Republic of Korea)፥ ከካርቱም ዩኒቨርስቲ (ሱዳን)፥ ከትሮፒካል እንስሳት ዘረመል እና ጤና ማዕከል (CTLGH) (ስኮትላንድ)፥ ከስዊድን የግብርና ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ (ስዊድን) እና ከኖቲንግሃም ዩኒቨርሲቲ (እንግሊዝ) በተውጣጡ ተመራማሪዎች ተከናውኗል።

«ይህ ጥናት. . .» ይላሉ የዚህ ጥናት አስተባባሪ የሆኑትና በዓለም አቀፍ የእንስሳት ምርምር ኢንስቲትዩት (ILRI) መሪ ተመራማሪ እንዲሁም በኖቲንግሃም ዩኒቨርሲቲ የዘረመል ፕሮፌሰር እና በCTLGH የፕሮግራም መሪ (program leader) የሆኑት ፕሮፌሰር ኦሊቪዬ ሃኖቴ (Olivier Hanotte)። «ይህ ጥናት በመጭው ጊዜያት በአፍሪካ የሚገኙት የዳልጋ ከብቶች እንደ ምዕራባዊያን በወተት እና በስጋ ምርታማነት እንደሚታወቁት የዳልጋ ከብቶች ሁሉ ዕምቅ ህብረ ባህርያታቸው (mosaic of traits) ከወተት እና ስጋ ምርታማነት በተጨማሪ ችግሮችን መቋቋም የሚያስችሉ ዝርያዎችን ለማራባት ግንዛቤ ይሰጣል» ሲሉ ተናግረዋል። ፕሮፌሰር ሃኖቴ እና ባልደረቦቻቸው «ዘረመልን በአዝማናት ቅኝታቸው (Genomic Time Travel)» ለመጀመሪያ ጊዜ የሳይንስ ጠቢባን የአፍሪካ የዳልጋ ከብቶች ሁለንተናዊ የመላመድ አቅም እንዲኖራቸው(adaptable) ያስቻላቸውን የዘረመል ህብረህዋሳት መሰረት እንዲከልሱ አስችሏቸዋል።

የምርምሩ ተሳታፊ የሆኑትና በስዊድን የግብርና ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ (ስዊድን) የድህረ-ዶክትሬት ዲግሪ ተመራማሪ እንዲሁም በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ መምህር የሆኑት ዶ/ር ጌትነት መኩሪያው ታረቀኝ እንዲህ ይላሉ። «በልጅነቴ ከብቶችን በማግድበት ወቅት አባቴ ‘ለከብቶቹ የሚጠብቁብህን ዋጋ ሁሉ ክፈል፣ ይህን በማድረግህ በምላሹ እነሱ እራሳቸውን ይሰጡሀል' ይለኝ ነበር። ከዘመናት በኋላ ተመራማሪ ስሆን እንስሳትን ዋጋ በሰጠናቸው ቁጥር የበለጠ ከዘረመል ዳራቸው መነሻ ያደረገውን ልዩ መራሔ ባህሪ በመረዳት ምን ይህል ለህይወታችን አስፈላጊ እንደሆኑና እራሳቸውን እንደሚከፍሉን ተገነዘብኩ» ይላሉ ዶ/ር ጌትነት ።

በዓለም ዓቀፉ የእንስሳት ምርምር ተቋም (ILRI) መሪ ተመራማሪ ሆነው እየሰሩ ያሉት እና የአፍሪካ የእንስሳት ባለሙያዎች ማህበር ፕሬዝዳንት የሆኑት ሌላው ኢትዮጵያዊ የምርምሩ ተሳታፊ ዶ/ር ታደለ ደሴ “የአፍሪካዊያን የህይዎት መስተጋብር እንስሳት ላይ መሰረት የማድረጋቸው ሚስጥሩ እንስሳቱ በዘመናት

ሂደት ውስጥ የራሳቸውን መራሔ ባህሪያት እንዲያዳብሩና ተፈጥሯዊ ችግሮችን እንዲቋቋሙ ያስቻላቸው መሆኑ ሲሆን ይህም ወደፊት በሌላው ዓለም ሁሉ ተመራጭ ያደርጋቸዋል" ይላሉ።

በዓለም ዓቀፉ የእንስሳት ምርምር ተቋም (ILRI) የላይቭጅን ፕሮግራም (LiveGene program) ኃላፊ እንዲሁም የ "CTLGH" ም/ዳይሬክተር የሆኑት የምርምሩ ተሳታፊ የሆኑት ዶ/ር ስቲቭ ኬምፕ (Steve Kemp) ስለ አፍሪካ የዳልጋ ከብቶች ዘረመል ሁለንተናዊ አቅም ሲናገሩ "የእስያ የዳልጋ ከብቶች ከእስያ አህጉር ከ750 እስከ 1050 ዓመታት አካባቢ ምስራቅ አፍሪካ በደረሱ ጊዜ በተከሰተው "የዝግመተ ለውጥ ንዝረት (evolutionary jolt)" የአፍሪካን አስቸጋሪ የአየርና አካባቢ ተላምደው እንዲኖሩና መራባት እንዲችሉ አስችሏቸዋል" ብለዋሉ።

የአፍሪካ አርብቶ አደሮች ዜቡ (Zebu) በመባል የሚታወቁትን የእስያ ከብቶች ታውሪን (Taurine) በመባል ከሚታወቁ የአካባቢው ከብት ዝርያዎች ጋር ማራባት መጀመራቸውን የሙሉ ዘረመል ትንተናው (whole genome sequencing) ውጤት ያሳያል። በተለይም ዜቡ በአፍሪካ ዳልጋ በተለመዱት ሞቃታማና ደረቅ የአየር ጠባይዎች ውስጥ የዳልጋ ከብቶች እንዲኖሩ የሚያስችሏቸውን ባሕርያት አዋጥተዋል ፡፡ ነገር ግን ሁለቱን በማዳቀል ብቅ ያሉት አዳዲስ እንስሳት እንዲሁ እንደ ገንዴ ያሉ በተሸካሚ ነፍሳት የሚተላለፉ በሽታዎች (vector-borne diseases) የተለመዱባቸው እርጥበታማ የአየር ጠባይዎችን ለመቋቋም የታወሪዎችን አቅም ወርሰዋል ፡፡

"የቁም ከብት- በተለይም የዳልጋ ከብቶች - አከራካሪ ሊሆኑ ይችላሉ ፣ ነገር ግን ያለ እነሱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አፍሪካዊያን ገንቢ ንጥረ ምግብ (protein) ለማግኘት የዱር እንስሳትን ለማደን ይገደዱ ነበር" ይላሉ በዓለም ዓቀፉ የእንስሳት ምርምር ተቋም መሪ ተመራማሪ እና የ "African Dairy Genetic Gains program" አስተባባሪ የሆኑት ሌላኛው የጥናቱ ተሳታፊ ዶ/ር አሊይ አኬዮ ምዋይ (Ally Okeyo Mwai) ፡፡ "ይህም …" ይላሉ ዶ/ር ምዋይ ሲቀጥሉ "ለአፍሪካ አካባቢያዊ ስነምህዳር እና እጅግ አስደናቂ ለሆኑ የዱር እንስሳት ብዝሀነት ብዝበዛ ይሆን ነበር ፡፡"

የአፍሪካ የዳልጋ ከብቶች እየጨመረ የሚሄደውን የወተት እና የስጋ ፍላጎትን በዘላቂነት ለማርካት እንዲችሉ ያደረጓቸውን የተፈጥሮ ዘረመል ስጦታዎች በሙሉ መጠቀሙ አስፈላጊ ሆኖ ፣ የእንስሳት ምርት መጨመር ሊያመጣ የሚችላቸውን አሉታዊ ተጽዕኖዎችን መቀነስ ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በአፍሪካ ውስጥ ለሚገኙ

ብዙ አባወራ ቤተሰቦች በተለይም በጣም ድሃ የሆኑት በአጠቃላይ የቁም ከብቶች በተለይም የዳልጋ ከብቶች የቤተሰብ በጣም ጠቃሚ ሀብት ሆነው ይቀጥላሉ ፡፡ እንደ ትምህርት ቤት ክፍያዎች ላሉት ነገሮች ለመክፈል ከገቢው ጎን ለጎን የፕሮቲን እና የማይክሮ ንጥረ ነገር ምንጭ ይሰጣሉ ፡፡ በተጨማሪም ለሰብሎች ፍግ/የተፈጥሮ ማዳበሪያ ምንጭ በመሆን ሲያገለግሉ ፣ አንዳንድ የአፍሪካ የዳልጋ ከብት ዝርያዎች ደግሞ የምግብ ሰብሎች መደገፍ በማይችሉ ሁኔታዎች ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ ፣ ይህም ለአርሶ አደሮች የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የሚያስችል የመላመድ ስትራቴጂ አማራጭ ይሰጣሉ ፡፡

ፕሮፌሰር ሃኖቴ "አርብቶ አደሮች እንደዚህ አይነት ችሎታ ያላቸው አርቢዎች በመሆናቸው ዕድለኞች ነን" ይላሉ ፡፡ ይኸውም “በአፍሪካ የእንስሳት ምርታማነትን ከመቋቋም እና ዘላቂነት ጋር ለማጣጣም በ ILRI እና በሌሎችም አካባቢዎች ለሚከናወኑ ጥረቶች ጠቃሚ ፍኖተ ካርታ አበርክተዋል፡፡” በማለት ፕሮፌሰሩ ይገልጻሉ።

በሌላ በኩል ዶ/ር ኬምፕ “ለአካባቢ ተስማሚነት ማራባት ለአፍሪካ ስኬታማ የእንስሳት እርባታ ቁልፍ እንደነበር የአገረሰብ የዳልጋ ከብቶችን ህብረህዋሳት በማጥናት ማየት ይችላሉ” ይላሉ ፡፡ ሲቀጥሉም “ለወደፊቱ ምርታማ እና ዘላቂ እንስሳትን ለማዳበር ወደፊት በሚደረገው ጥረት ያ እውነታ መሆን አለበት ፡፡ ይሁንና ግቡ ንጹህ ዝርያን ማራባት ከሆነ ፣ ለመጥፋት ወይም ለውድቀት ተዘጋጅተዋል እንደማለት ነው” ሲሉ ያክላሉ።

የዓለም ዓቀፉ የእንስሳት ምርምር ተቋም (ILRI) ዋና ዳይሬክተር የሆኑት ዶ/ር ጂሚ ስሚዝ (Jimmy Smith) “የእንስሳት እርባታ ለአፍሪካ ማህበረሰብ ጤና እና ሀብት ዘላቂነት ወሳኝ ሚና እንደነበረውን እየተጫወተ እንደሆነ መረዳቱ ጠቃሚ ነው” ብለዋል ፡፡ ዋና ዳይሬክተሩ አክለውም “ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገራት የእንስሳት እርባታ ዘላቂ መንገድን ለመንደፍ የቀደሙ ጥረቶችን ያስቀጠለው የመቋቋም ችሎታ እርባታ ላይ ያተኮረ ስራ መስራት መሰረታዊ ተግባር ነው” ሲሉ ይጠቁማሉ፡፡

##

ዓለም አቀፍ የእንስሳት ምርምር ተቋም (ILRI) ለትርፍ ያልተቋቋም በዝቅተኛ እና መካከለኛ ገቢ ባላቸው አገራት ውስጥ ያሉ ሰዎች በታዳጊው ዓለም በመለስተኛ የአነስተኛ እርሻ እና ኢንተርፕራይዝ የጀርባ አጥንት ሆነው በሚቀጥሉት እንስሳት ህይወታቸውን ፣ ኑሯቸውን እና መሬቶቻቸውን እንዲያሻሽሉ የሚረዳ ተቋም ነው ። ILRI የ CGIAR የምርምር ማዕከላት አካል የሆነና በኬንያ እና በኢትዮጵያ ዋና መቀመጫውን ያደረገ ተቋም ሲሆን በአፍሪካ እና በእስያ አገሮች ሌሎች 14 ቢሮዎች አሉት ።

**ምስጋና**

ይህ ሥራ ከ Grant from the Next-Generation BioGreen 21 ፕሮግራም እና Post-Genome ፕሮጀክት (Project Nos. PJ01323701 እና PJ01040601) ፕሮጀክት ፣ ከኮሪያ ሪፐብሊክ የገጠር ልማት አስተዳደር በተገኘ ድጋፍ ተሰርቷል። የዳልጋ ከብት ዝርያዎች ናሙና በ CGIAR የእንሰሳት እና ዓሳ CRP (ኡጋንዳ እና ኢትዮጵያ) ፣ በካርቱም ዩኒቨርሲቲ (ሱዳን) እና በብሔራዊ የባዮ ቴክኖሎጂ ልማት ኤጀንሲ (NABDA) (ናይጄሪያ) ድጋፍ ተደርጓል ። የሚከተሉት ተቋማት እና ሰራተኞቻቸው ለአፍሪካ የዳልጋ ከብቶች ናሙና ድጋፍ አድርገዋል-ILRI ካፒቲ ራንች; የእንስሳት ሀብት እና ዓሳ ሀብት ሚንስቴር  (ሱዳን); ኦል ፔጄታ ጥበቃ (ኬንያ); የብዝሃ ሕይወት ኢንስቲትዩት (ኢትዮጵያ); እና የእንስሳት ጤና አጠባበቅ ዳይሬክተሮች እና የቀህድ ከብት ጠባቂዎች ከኢትዮጵያ ፣ ኬንያ ፣ ኡጋንዳ እና ሱዳን ናቸው ። የ ILRI የእንስሳት ዘረመል መርሃግብር በ CGIAR የምርምር ፕሮግራም በእንሰሳት (CRP ከብት) የተደገፈ ሲሆን ለ CGIAR Trust Fund (http://www.cgiar.org/about-us/our-funders/) አስተዋፅዖ አድራጊዎች በሚደገፈው ይህ ምርምር በከፊል በቢል እና ሜሊንዳ ጌትስ ፋውንዴሽን እና ከእንግሊዝ የውጭ እርዳታ ፣ ከኮመንዌልዝ እና ልማት ጽ / ቤት (Grant Agreement OPP1127286) በጋራ የገንዘብ ድጋፍ የተደረገለት በCTLGH የኤዲንብራ ዩኒቨርሲቲ ፣ ኤስ.አር ዩ.ሲ (የስኮትላንድ ገጠር ኮሌጅ) እና ዓለም አቀፍ የእንሰሳት ምርምር ኢንስቲትዩት ።